# "እኔ፡ ማን ነኝ? ምንድር ነኝ?" በሚል ርእስ፡ በፌስቡክ፡ የጎዋ-መገናኛ መድረክ፡ በሦስት ክፍል ተዘጋጅቶ የቀረበ መጠነኛ ማብራሪያ።

## የመጀመሪያ ክፍል፤

እኛ፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ የአንድ እናት እና የአንድ አባት ልጆች መኾናችንን ለመግለጽ የምንጠቀምበት፡ "ወንድሜ"፣ ወይም፡ "ወንድምዬ"፣ "እኅቴ"፣ ወይም፡ "እኅትዬ" የሚሉት የተዘምዶ ስሞች፡ ትክክለኛ ትርጓሜያቸውን እንደምናውቅ ይታመናል፤ ይኸውም፡ "ወንድም" የሚለው፡ የኢትዮጵያኛ ቃል፡ "ወልደ-እም" ከሚለው የግእዝ ሓረግ የተወረሰ ሲኾን፥ ፍቺው፡ የ"እናት-ልጅ" ማለት ነው፤ "እኅት" የሚለው የግእዝ ቃል ደግሞ፡ ቀጥተኛ ትርጓሜው፡ "በሴትነት አካልና ባሕርይዋ፡ የእናት አምሳያ የኾነች!" ተብሎ ይፈታል።

እውነታው ግን፡ እኛ፡ ርስ በርሳችን፡ "እኅትማማቾች" እና "ወንድማማቾች" ያለመኾናችን፡ የተፈጥሮ ትንግርት እና እውነታ ነው። ይኸም እውነታ የሚጐላው፡ "እኔ"፡ የምለው ማንነቴ፡ ማን ነው? ምንድር ነው? ወንድሜስ ማን ነው? እኅቴስ ማናት? ለሚሉት ተያያዥ ጥያቄዎች፡ አግባብ ያለውን ተመጣጣኝ ምላሽ በመስጠት ነው።

"እኔ"፡ የሚለው ቃል የሚያመለክተው፡ ግዙፉን፡ ፍጥረታዊ አካላችንን ሳይኾን፡ "እኔ፡ ማነኝ?" ብሎ መጠየቅ የሚችለውን፡ "ለባዊና ነባቢ፡ ማለትም፡ አመዛዛኝ ባለዐምሮና ተናጋሪ ባለቃል የኾነውን፡ ሕያው፡ የነፍስ አካላችንን ነው!"። የእዚህም እውነታ፡ "እኔ"፡ የሚለው ቃል፡ "አንተ"፣ ወይም፡ "አንቺ" እንደተባሉት የስም ምትኮች፡ የ"ወንድ"፣ ወይም፡ የ"ሴት" አንቀጽን ለይቶ የሚያመለክት ሳይኾን፡ የሚወክለው፡ "ኢጾታዊ (Genderless) ባሕርይን" በመኾኑ፡ ይታወቃል፤ ይረጋገጣል። ያ፡ "እኔ"፡ የምንለው ኢጾታዊ አካልና ባሕርይ ነው፡ ገላ-ዐፈርን ለብሶ፡ በወንድና በሴት ጾታነት የተገለጸው።

ያ "እኔ"፡ የምንለው፡ የሚኖረውንና እየኖረ ያለው፡ የራሳችን አካልና ባሕርይ አድርገን የምንቈጥረው፡ "እኔ፡ የምንለው ማንነትም"፡ "ማን ነህ?" ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ፡- "**አነ ውእቱ ዘሀለውኩ ወእሄሉ!**"፡ "**ያለሁና የምኖር እኔ ነኝ!**" ብሎ ትክክለኛውን ምላሽ አስገኝቶልናል። ያም፡ "ያለሁና የምኖር እኔ ነኝ" ያለው አካል፡ "እግዚአብሔር ነው!"። "ያለ፡ እግዚአብሔር ነው!"፣ "የሚኖር፡ እግዚአብሔር ነው!"፣ "'እኔ፡ እየኖርሁ ነው! ብለን የምናስበው፡ እኔነታችን አይደለም እየኖረ ያለው! እግዚአብሔር ነው! ከእግዚአብሔር ሌላ፡ ምንም ምን፡ ኢምንት ስንኳ የለም።" (ዘጸአት ፫፣ ፲፫-፲፭።)

ለእዚህ ነው፡ የእውነት አርበኛው፡ ኢትዮጵያዊው ኢዮብ፡-

**"ርሱ፡ ልቡን፡ ወደራሱ ቢመልስ፥ መንፈሱንና እስትንፋሱን፡ ወደራሱ ቢሰበስብ፡ ሥጋ ለባሽ ኹሉ በአንድነት ይጠፋል፤ ሰውም፡ ወደዐፈር ይመለሳል።"** ያለው። (ኢዮብ ፴፬፣ ፲፬።)

አዎን! ሰው፡ በሥጋዊ አካሉና ባሕርይው፡ በእስትንፋሱ እየተነፈሰ፣ በነፍሳዊ አካሉና ባሕርይው፡ በልቡ እያወቀና እያገናዘበ፥ በመንፈሳዊ አካሉና ባሕርይው ደግሞ፡ በመንፈሱ ዘለዓለማዊነት እየኖረ ያለው፡ በእግዚአብሔር ሕይወት ነው፤ የሚተነፍስበት እስትንፋስ፡ እግዚአብሔር ነው፤ የሚራቀቅበት ለባዊ አምሮ፡ እግዚአብሔር ነው፤ ሕያው መንፈሱም፡ እግዚአብሔር ነው።

አዎን! ስለዚህ፡ ያለ፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው! የሚኖር፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው! እየኖረ ያለ፡ እግዚአብሔር ብቻ ነው! "አንቺ"፣ "አንተ"፡ "አናንተ"፣ "እኛ" የሚባሉ፡ ኩነቶች የሉም። "እኔ"፡ የምንለውም፡ ያለ ማንነት፡ "እግዚአብሔር ብቻ ነው!"።

በጾታ፣ በመልክ፣ በቀለም፡ በተፈጥሮ ኅብሮች የተለያየን ቢመስለን፡ **"ዘርእየ ኪያየ፡ ርእዮ ለአብ! ...በከመ አነ፡ በአብ፤ ወአብ፡ ብየ!"** ማለትም፡ **"እኔን ያየ፡ አብን አይቷል! ...እኔ፡ በአብ እንዳለሁ፥ አብም፡ በእኔ አለ!"** እንዲሁም፡ **"አንተ፡ አባት ሆይ፡ በእኔ እንዳለኽ፡ እኔም ባንተ፡ እነርሱ ደግሞ፡ በእኛ፡ አንድ ይኾኑ ዘንድ እለምናለኹ።"** እንዳለ፡ ሌላውም ፍጥረተ-አካል፡ "አንዱ፣ በአንዱ ውስጥ ህልው ኾኖ አለ!"፤ ያ፡ ህላዌና አንድነትም፡ "እግዚአብሔር ነው!"። (ዮሐንስ ፲፯፣ ፳፩።)

ስለዚህ! ርስ በርሳችን ልንጠራራ የሚገባው፡ ወንድምዬ፣ ወይም፡ እኅትዬ በሚል የተዘምዶ (የዝምድና) ስም ሳይኾን፡ "እኔ"፣ "እኔዬ"፣ ወይም፡ "እኔነት" በሚል፡ የባሕርይ ስም ሊኾን ይገባል። ምክንያቱም፡ ያለው፡ ፩ እግዚአብሔር ነው፤ ያ፡ ያለ፡ አንድ ማንነት፡ በተለያየ፡ የፍጥረት አካልና ባሕርይ ቢገለጽም፡ ኹለት፣ ወይም፡ ሦስት አይኾንም፤ ነቍ (ምንጩ) አንድ ነውና፤ ራሱንም፡ "እኔ" ብሎ ይጠራል እንጂ፡ ማንም፡ "እራሱን"፡ እኅቴ፣ ወይም፡ ወንድሜ ብሎ አይጠራም።

## ኹለተኛ ክፍል፤

ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "እኔ" ስለሚለው ማንነትና ምንነት፡ በልባቸው ባለው የእውቀት ዛፍ አማካይነት፡ በቅጡ ተረድተውትና ተገንዝበውት፡ በበቂም አውቀውትና አምነውበት፡ በመጨረሻም፡ በምግባር በመግለጽ፡ ለመልካሙ የሕይወት ዛፍነት አብቅተውት ኖረዋል። በቅዱሳት መጽሓፍት፡ ደጉን ከክፉ ለይቶ የሚያሳውቀው፡ "ዕፀ-እውቀት (የእውቀት ዛፍ)" እና ለዘለዓለም በሕያውነት የሚያኖረው፡ "ዕፀ-ሕይወት (የሕይወት ዛፍ)"፡ ፍሬያቸው ተቈርጦ፡ ለግብዓተ-ምግብነት የሚውሉ ግዙፋን ዕፅዋት ብቻ ሳይኾኑ፡ "አነ ውእቱ ዘሀለውኩ ወእሄሉ"፡ "ያለሁና የምኖር እኔ ነኝ" ያለው፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር ነው።

በአገራችን፡ በልዩ ልዩ ቦታ፡ ስሙን፡ "ዋቃ" ብለው የሚጠሩትና "በወርካ ዛፍ ላይ በሕያውነት አለ!" ብለው የሚያምኑት እግዚአብሔር፥ እንዲሁም፡ ለዚያ ሃይማኖታቸው፡ መሠረትና መነሻ፡ እነዚህ፡ "ዕፀ-እውቀት" እና "ፅፀ-ሕይወት" የተባሉት ዛፎች መኾናቸው፡ ከቶውኑ አያጠራጥርም። "ዋቃ" የሚለውም፡ "ጄቃ"፣ "ቤቃ"፣ እንደምንለው፡ ትርጒም ያለው፡ አማናዊ፡ የእግዚአብሔር ስም መኾኑ፡ ሊሠመርበት ይገባል።

ወደቀደመው ነገር እንመለስና፤ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ እንደራሳቸው፡ በሀብት የበለፀገ ሰውን ይቅርና፡ ከአንዳቸው ስንኳ፡ በሥጋዊ ሀብት ደረጃ፡ ያነሰ መስሎ የታያቸውን ግለሰብ ስንኳ፡ "እኔ" ብለው፡ የሚጠሩት መኾኑ የታወቀ ነው፤ ይህንንም፡ በሙሉ አጠራር፡ "የእኔ-ቢጤ" በማለት ይገልጹታል። "ቢጤ" ማለት "ቢጽየ" ከሚለው የግእዝ ቃል የተወሰደ ሲኾን፡ ፍቹው፡ "ከእራሴ ጋር ትክክል የኾነ አንድነት!" ማለት ነው።

የዚህንም እውነታ፡ እንዲህ በሚሉት፡ የእግዚአብሔር ቃላት፡ አጒልቶ ማሳየት ይቻላል።

ይኸውም፡

"አማን እብለክሙ! ኵሎ ዘገበርክሙ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ እለ የአምኑ ብየ፡ ሊተ ገበርክሙ።" ማለትም፡ "እውነት እላችኋለሁ፡ ከኹሉ ከሚያንሱ ወንድሞቼ፡ ከእነዚህ፡ ለአንዱ፥ ወይም፡ ለአንዲቱ ያደረጋችሁት (በጎ ነገር) ኹሉ፡ ለእኔ አደረጋችሁልኝ!"

እንዲሁም፡

**"አማን እብለክሙ! ዘኢገበርክሙ፡ ለአሓዱ፡ እምእሉ ንኡሳን አኀውየ፡ ሊተ ኢገበርክሙ።"**

ማለትም፡

**"እውነት እላችኋለሁ፡ ከኹሉ ከሚያንሱ፡ ከእነዚህ፡ ለአንዱ፥ ወይም፡ ለአንዲቱ ስላላደረጋችሁት (በጎ ነገር)፡ ለእኔ አላደረጋችሁልኝም!"** የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው። (ማቴ. ምዕራፍ ፳፭።)

በእዚህ የእውነት ቃል አማካይነት፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጡሮቹ፡ በገሓድ ያሳወቀው እውነት ቢኖር፡ አንድና አንድ ኾኖ ይገኛል፤ ያም፡

> 'ከማንኛውም፡ ሰብአዊ ፍጥረቴ፥ እንዲሁም፡ የሚኖሩበት ማሕበረሰብ፡ "ንዑሳን"፣ ወይም፡ "ዝቅተኛ" ብሎ በፈረጃቸውና ባገለላቸው ምስኪን ፍጥረቶቼ እንኳ ሳይቀር፡ በእነርሱ ሰውነት ተገልጬ፡ በልቼ፡ የምጠግበው፣ ወይም፡ አጥቼ፡ የምራበው፣ ጠጥቼ፡ የምረካው፣ ወይም፡ አጥቼ፡ የምጠማው፣ ቤት አግኝቼ፡ የምጠለለው፣ ወይም፡ ተቸግሬ፡ የምንከራተተው፣ ልብስ ኖሮኝ፡ የምጐናጸፈው፣ ወይም፡ ቸግሮኝ፡ የምራቈተው፣ ጤና አግኝቼ፡ ሰላም የምኾነው፣ ወይም፡ ጤና አጥቼ፡ የምታመመው፣ ፍትሕ አግኝቼ፡ በነፃነት የምኖረው፣ ወይም፡ ፍትሕ አጥቼ፡ የምንገላታው፣ ወይም፡

የምታሠረው፡ ይህን ኹሉ ነገር የምኾነው፡ "እኔ ነኝ!" ማለቱ መኾኑ፡ ሊካድና ሊታበይ የማይችል ሓቅ ኾኖ፡ ዓለሙን ይፋረደዋል።

ያለ/ያለች፣ በፍረታተ-ዓለማቱ ባሕርይና አካል ኹሉ ተገልጦ/ተገልጣ፡ በሕያውነት የሚኖር/የምትኖር ማንነት፡ "እግዚአብሔር ብቻ ነው/ናት!"።

## ሦስተኛ ክፍል፤

"እኔ፡ ማነኝ?"፣ "እኔ የምለውስ፡ እኔነቴ፡ ማን ነው? ምንድን ነው" በሚለው፡ የሕይወት ጥያቄና ፍለጋ ውስጥ፡ "ሥነ-ፍጥረት" የምንላት ብርቅዬ ትንግርት፡ ምነቷንና ማንነቷን፡ እንደጥሩ፡ የምንጭ ውኃ ኵልልና ፍንትው አድርጋ፡ ራሷን፡ ገላልጻ ከማሳየቷ በላይ፡ የተፈጥሮ ድምፆቿን ከፍ አድርጋ፡ ወዝ ባለው ርቱዕ አንደበቷ፡ "ኑ! ከእኔ ተማሩ! አካኼዳችሁን አቅኑ!" በማለት፡ የሕይወት ልምዷን ታካፍለናለች።

"እኔ የምለው፡ እኔነቴ፡ ማን ነው? በሚለው ፍለጋ ውስጥ፡ የሥነ-ፍጥረትን፡ መልካም ድምፅዋን ከሠሙላት፡ ደቀ-መዝሙሮቿና ተማሪዎቿ መካከል፡ አንደኛው አገልጋይዋና ተገልጋይዋ፡- "(የፈጣሪያችን እግዚአብሔር)፡ የማይታየው ባሕርይ፡ እርሱም፡ የዘላለም ኃይሉ፣ ደግሞም፡ አምላክነቱ፡ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት፡ (ማለትም፡ በሥነ-ፍጥረት ውስጥ ተጠቃልለው በሚገኙት ፍጥረታት ውስጥ)፡ ታውቆ ግልጥ ኾኖ ይታያል!" በማለት መስክሮላታል። (ሮሜ. ፩፣ ፲፱-፳።)

አዎን! እኛም፡ ከእዚህ፡ የእውነት ቃል፡ የምንቀስመው አያሌና በርካታ ቍምነገሮች ይገኛሉ፤ እነዚህም፡-

፩ኛ፤ እግዚአብሔር፡ በሥነ-ፍጥረት ውስጥ ግልጥ ኾኖ የሚታይ ብቻ ሳይኾን፥ በፍጥረት ውስጥ፡ ህልው ኾኖ፡ በሕያውነትና በዘለዓለማዊነት የሚኖር መኾኑ

፪ኛ፤ ሥነ-ፍጥረት፡ እግዚአብሔር፡ ለፍጡሮቹ ኹሉ መልካካም አኗኗር ሲል፡ ራሱን፡ በርቅቀትና በግዝፈት፣ በስፋትና በምልዓት የገለጠበት ኵነት መኾኑ

፫ኛ፤ "እግዚአብሔር" ማለት፡ "ሥነ-ፍጥረት"፣ "ሥነ-ፍጥረት" ማለት፡ "እግዚአብሔር" መኾኑ

፬ኛ፤ በእግዚአብሔር አምሳል፡ መርገፍ (ምሳሌ) ብቻ ሳይኾን፡ "አዳም ኮነ፡ ከመ አሓዱ እምኔነ!" ማለትም፡ "አዳም፡ ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ተብሎ፡ "እግዚአብሔርን

ኾኖ!" ለመፈጠር የታደለው "አዳም (ሰው)"፡ በዚህ፡ እግዚአብሔራዊ የፍጥረት ባሕርይው፡ ራሱ፡ ሥነ-ፍጥረት መኾኑ

፭ኛ፤ አንዱ፡ የሥነ-ፍጥረት አካል የኾነችው ምድር፡ አዳምን፡ በእናትነቷ፡ መሬታዊ ሥጋዋን አልብሳ፡ አርግዛ የወለደችው ብቻ ሳትኾን፤ ወይም፡ ከእናትነት ጉያዋ ሳትነጥል፡ በሞግዚትነት የምትጠብቀውና የምትንከባከበውም ብቻ ሳይኾን፥ አቻ በሌለው የእናትነት ፍቅሯ፡ የምትበላውን እያበላች፥ የምትጠጣውንም እያጠጣች፤ የምትተነፍሰውንም እያስተነፈሰችው፡ ከቅድስት ማኅፀኗ ሳታወጣውና ሳትለየው፡ በመቅደሷ ውስጥ የምታኖረው መኾኑ

፮ኛ፤ ይህችም ቅድስት ምድርና መሬት፡ እግዚአብሔር፡ ራሱን የገለጠባት ኹነት ስትኾን፡ በተለይ፡ በሴትነት፤ ወይም፡ በእናትነት አካልና ባሕርይዋ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗ

፯ኛ፤ "አንተ የቆምህባት ስፍራ፡ የተቀደሰች መሬት ናትና፡ ጫማህን፡ ከእግርህ አውጣ!" ከሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል ጋር፥ የቀደሙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ መሬትን፡ ያለጫማ፡ በባዶ እግራቸው በመርገጥ፡ ምድር፡ የድንግል ማርያም ሰውነት ስለመኾኑ ማስመስከራቸው (ዘጸ. ፫፤ ፭።)

፰ኛ፤ የሰው ሰውነት፡ በተለይ፡ ሥጋዊ አካሉና ባሕርይው፡ በአጭር ቍመትና በጠባብ ደረት ሳይወሰን፡ ባጠቃላይ፡ የተገኘባት መላው ምድር፡ ሰውነቱ መኾኗ

፲ኛ፤ ለዚህም እውነታ፡- በመሬት ላይ ገዝፈው የሚታዩት ዛፎች፥ በውስጥ አካላችን ከሚገኙት ሳንባዎቻችን ጋር፡ በትንፋስ አመንጭነታቸውና በአካላዊ ቅርጻቸው አንድና ተመሳሳይ በመኾናቸው፡ በግዘፍ የምናያቸው ዛፎች፡ በእውን፡ የሳንባ አካላችን የመኾናቸው እውነታና የመሳሰሉት ይገኙበታል።